


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## ጅማሬአችን ብቻ ሳይሆን፥ መጨረሻችንም ያማረ ይሁን

**በቃል የሚጠና፦ 2ኛ ጢሞቴ. 4፥7-8**

***"ይህን መልካም ሥራ በእናንተ ሕይወት ውስጥ የጀመረ አምላክ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመለስበት ቀን ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ" (ፊል. 1፥5-6።)***

### 1 ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት ምክንያት ነበረው

ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩት። ከምክንያቶቹ አንደኛው የፊልጵጵዩስ አማኞች የነበራቸው የእምነት አቋም ወይንም መንፈሳዊ ዕድገት ነበር። ስለ እነርሱ ሲያስብ ልቡ በልዩ በደስታ ስለሚሞላ እግዚአብሔርን በጣም ያመሰግን ነበር። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ አማኞች ሕይወት ደስ ይበለው እንጂ፥ ሁሉም መልካም ነው በማለት ፍጹም ረክቶ የተቀመጠ አልነበረም። ገና ብዙ እንደሚቀራቸው ያውቃል። መጨረሻቸው እንደ አጀማመራቸው ያማረ ላይሆን ይችላል ብሎ በማሰብ ይመስ ላል፥ *"ይህን መልካም ሥራ በእናንተ ሕይወት ውስጥ የጀመረ አምላክ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመለስበት ቀን ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ"* በማለት ምኞቱንና ፍላጎቱን የገለጸው። በመንፈሳዊ ሕይወት እንደገና መወለዳችን ብቻ በቂ አይደለም። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደግና መብሰል ያስፈልገናል። ሰው እንደገና በተወለደበት ቀን ከእግዚአብሔር የሚገኘውን በረከት ሁሉንም አያገኝም። እያደገ በሄደ ቁጥር የሚያገኛቸው በረከቶች ብዙዎች ናቸው። እርግጥ ነው እንደ ገና መወለድ፥ እግዚአብሔር ለሚሰጠው ቁጥር ስፍር ለሌለው ሰማያዊ በረከት መጀመሪያ፥ ወይንም መግቢያ በር ነው። ጳውሎስ "እግዚአብሔር የፊልጵስዩስ አማኞችን በመልካም ሥራ እንዳስጀመራቸው፥ ክርስቶስ እንደገና እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ መልካም ሥራውን በሕይወታቸው መሥራቱን እንደሚቀጥል አምናለሁ ይላል።

### 2 ትክክል ያልሆኑ የክርስትና አቋሞች

ዛሬ በክርስቲያኖች መካከል ትክክል ያልሆኑ ሁለት ዓይነት አቋም የያዙ ክፍሎች እንዳሉ እናያለን። ይኸውም፥

#### (ሀ) *ሳይወለዱ ለማደግ የሚሞክሩ*

ሰው በሥጋዊ ተፈጥሮው፥ እስከ መጨረሻው ድረስ፥ ወይንም ሙሉ የሆነ የዕድገት ደረጃ ለመድረስ፥ መጀመሪያ መወለድ ያስፈልገዋል። ሳይወለድ ማደግ አይችልም። ጽንስ በእናቱ ማህጸን ተጸንሶ ዘጠኝ ወር ማህጸን ውስጥ በመቆየት ካደገ በኋላ፥ ጊዜው ሲደርስ ይወለዳል። ከዘጠኝ ወር በኋላ ያ ጽንስ የማይወለድ ከሆነ ግን፥ ቤተሰቡን ማሳሰብ ይጀምራል። በመጨረሻም በግድ በሀኪሞች እርዳታ ከእናቱ ማህጸን እንዲወጣ ይደረጋል። አንዴ ከተወለደ በኋላ ደግሞ፥ ዕድገትን የሚከለክል ልዩ በሽታ ከሌለበት፥ ወይንም ጤናማ የሆነ አካል ካለው፥ አስፈላጊውን ምግብና እንክብካቤ ሲያገኝ፥ ቀስ በቀስ ያድጋል። በሥጋ መወለድ እንዳለ ሁሉ፥ በመንፈስም መወለድ እንደሚያስፈልግ እናውቃለን። ሰው እንደ ገና ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት እንደማይችል ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ ነግሮታል። *"እውነት፥ እውነት እልሃለሁ፤ ሰው እንደገና ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም..."* (የዮሐ. 3፥3)።

ዛሬ በየቤተ ክርስቲያኑ እንደገና ያልተወለዱ፥ ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ብዙ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ዘመን በመቆየታቸው፥ በመዘመራቸው፥ አሥራታቸውን በመስጠታቸው፥ ሞቅ ያለ አምልኮ በማምለካቸው ብቻ፥ እንደ ገና የተወለዱ ክርስቲያኖች የሆኑ መስሎ የሚሰማቸው አሉ። ይሁን እንጂ፥ እንደ ገና ስላልተወለዱ፥ የሚፈለገው የሕይወት ለውጥ አይታይባቸውም። ሥርዓት በመፈጸማቸው ክርስቲያኖች ይምሰሉ እንጂ፥ በዕለታዊ ተግባራቸው አሁንም ዓለማውያን ናቸው። ዓለማውያን የሚያደርጉትን ሁሉ ያደርጋሉ። ይጠጣሉ፥ ዳንኪራ ቤት ሄደው ይጨፍራሉ፥ ካልሆነም በመዝሙሩ አስታከው ይደንሳሉ፤ ዝሙት ይፈጽማሉ፤ ይሰርቃሉ፤ ይዋሻሉ፤ ያጭበረብራሉ። በመንፈስ እንደገና ስላልተወለዱ፥ ከኃጢአት ልማዳቸው መላቀቅ ከባድ ይሆንባቸዋል። ጥሩ አጀማመር ስለሌላቸው፥ ጥሩ አጨራረስም አይኖራቸውም።

እርግጥ ነው ይጸልያሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ያነባሉ፤ ይጾማሉ። እነዚህ ሁሉ ለመንፈሳዊ ዕድገት ጠቃሚ ቢሆኑም፥ ይህንን ሁሉ እያደረጉ አያድጉም። ትልቁ ምክንያት እንደገና ስላል ተወለዱ፥ እውነተኛ የሕይወት ለውጥ ስለሌላቸው ነው። ለማደግ መጀመሪያ መወለድ ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን በእንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ስለተሞላች ነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ *"ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ይጀምራል"* ያለው። የፊልጵስዩስ ምዕመናን አጀማመራቸው ጥሩ ስለሆነ ነው ጳው ሎስ *"ይህን መልካም ሥራ በእናንተ ሕይወት ውስጥ የጀመረ አምላክ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመለስበት ቀን ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ"* ያላቸው።

## (ለ) *ተወልደው የማያድጉ*

ጥሩ ጀምረው በጥሩ የማይጨርሱ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ እንደገና ቢወለዱም፥ በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ ያቃታቸው ናቸው። ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞች *"እንደገና ከመወለድ"* ደረጃ በላይ ማለፍ እንደሚ ችሉ፥ እግዚአብሔር በዕድገት ሂደት ውስጥ እንደሚያስኬዳ ቸው፥ አንድ ቀን ክርስቶስ በሚመጣበትም ቀን እንደሚቀበ ላቸው እርግጠኛነቱን ይገልጻል። ተወልደው አንድ ቦታ የሚ ያቆሙ፥ በዕድገት ሂደት ውስጥ የማያልፉ፥ ሁልጊዜ "ሀ! ሁ!" ሁልጊዜ "ዳዴ" የሚሉ ክርስቲያኖች በዘመናችን ጥቂቶች አይደሉም። አጀማመራቸው ጥሩ ይሆንና፥ "የት ይደርሳሉ?" ተብለው ሲጠበቁ፥ ተደነቃቅፈው መንገድ ላይ ወድቀው የሚቀሩ ብዙዎች ናቸው።

ጳውሎስ *"እርግጠኛ ነኝ"* ሲል ለመሆኑ እርግጠኛነቱ በምን ይሆን? እርግጠኝ የሆነበት *አንደኛው "መልካም ሥራን"* ነው። መልካም *ሥራም*፥ የጸጋ *ሥራ*፥ ወይንም እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ውስጥ የሚፈጽመውን የነፍሱን ማዳን ወይንም ደህነትን ነው። እግዚአብሔር የሰጣቸው ደህ ንነት እስከ መጨረሻው ድረስ እንደሚቀጥል "እርግጠኛ" እንደሆነ ይናገራል። ጳውሎስ እርግጠኛ የሆነበት ሁለተኛው ነገር፥ *ያገኙት ለውጥ አንድ ቦታ እንደማይቆም፥ በዕድገት ሂደት ውስጥ እንደሚያልፍ ነው።* ማንኛውም ነገር "መጀመ ሪያ" እንዳለው ሁሉ፥ "መጨረሻም" ይኖረዋል። የሚያስጀ ምረው ሰው ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ነው። ያስጀመራቸው እግዚአብሔር ከሆነ፥ የሚያስጨርሳቸውም ሰው ሳይሆን፥ እርሱ ራሱ ነው። *ሥራ*ውም መልካም የሆነበት ምክንያት በሁ ሉም የዕድገት ደረጃ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱ ስላለበት ነው። መልካም *ሥራ* የሆነበት ሌላው ምክንያት፥ ሰውን ወደ በጎነት እንደሚያመጣው፥ የክርስቶስን መልክና ባህሪ በሕይ ወቱ ስለሚቀርጽበት ሲሆን፥ እንዲሁም እግዚአብሔርን የሚ ያስከብር በመሆኑ ነው።

*"ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመለስበት ቀን"* ሲል፥ ምን ማለቱ ነው? ሰው ከሞተ በኋላ ወደ ፍጹምነት ስለማይ ደርስ፥ ሙሉና ፍጹም መሆን የሚችለው *"ክርስቶስ ለፍርድ በሚመለስበት"* ጊዜ ብቻ እንደሆነ መግለጹ ነው። መልካሙን *ሥራ* የጀመረው አምላክ እርሱ በወሰነው ቀን፥ ማለትም ክርስቶስ በሚመለስበት ቀን ከፍጻሜ ያደርሰዋል። ሰው በስጋ ውና በነፍሱ በሙላት የሚከብረው፥ በቤዠው አምላክ ፊት መጨረሻ ላይ ሲቀርብ ብቻ ነው። ከሙሉ ክብር የሚደር ሰውም ሰው በራሱ ኃይልና ጉልበት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ፥ በክርስቶስ አማላጅነትና እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውስጥ ሁልጊዜ በመኖር ነው። ጳውሎስ ስለ ፊልጵስዩስ አማኞች ከላይ ባየነው ሁኔታ *"እርግጠኛ ነኝ"* ይበል እንጂ፥ ለእነርሱ ከመጸለይ፥ ከመምከርና ከማበረታት ያቋረጠበት ጊዜ የለም።

## 3 ከዚህ ክፍል የምንማረው ጠቃሚ ትምህርት

**(ሀ) እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ምክንያት አለን።**

እኛም እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔርን የም ናመሰግንበት ልዩ ልዩ ምክንያቶች አሉን። በሕይወታችን ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸው በጎ ስጦታዎች ብዙ ናቸው። የብዙዎቻችን ድካም የተደረገልንን፥ ያገኘውን በጎ ነገር በመ ቁጠር ፈንታ፥ ያላገኘነውን፥ ያልተሳካልንን መቁጠራችን ነው። ለጳውሎስ መንፈሳዊ ፍሬዎቹ የፊልጵስዩስ አማኞች ናቸው። ስለ እነርሱ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። እኛም በክርስቶስ በኩል ስላገኘናቸው፥ ወደ ክርስቶስ መንግሥት ስላመጣና ቸው፥ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባል።

**(ለ) ሳንወለድ ማደግ አንችልም።** ሳይወለዱ ማደግ እንደማ ይቻል ስናውቅ፥ በክርስቶስ እንደ ገና መወለዳችንን እርግጠ ኞች መሆን አለብን። የሃይማኖት ሥርዓት በመጠበቃችን ብቻ መንፈሳዊ መሆን አንችልም።

**(ሐ) እንደገና ከመወለድ ማለፍ አለብን።** በሥጋ ተወልደው፥ የማያድጉ ሕጻናት ወላጆቻቸውን ስጋት ላይ ይጥላሉ። በመንፈሳዊ ሕይወትም እንደገና ተወልደን፥ ማደግ ሲያቅተን፥ የቤዠንን ጌታ ቅር እናሰኛለን። በጥሩ ሁኔታ እንደገና የተወለዱ፥ ማደግ ግን ያቃታቸው ክርስቲያኖች በየአብያተ ክርስቲያናቱ ብዙ ናቸው። በእኛ ዘመን ብቻ ሳይሆን፥ በቀድሞ ቤተ ክርስቲያናትም ነበሩ። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን፥ ማደግ ያቃታቸውን አማኞች፥ *"..ሥጋውያን እንደመሆናችሁ መጠን ነው እንጂ መንፈሳውያን እንደመሆናችሁ መጠን ላስተምራችሁ አልቻልሁም..."* (1 ቆሮ. 3፥1-2) ይላቸዋል። ለማደግና ብዙ ፍሬ ለማፍራት ከጌታ ጋር የተጣበቀ ሕይወት እንዲኖረን ያስፈልጋል።

---




**የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።**

**(ኤፌሶን 6፥17)**




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

1. ጳውሎስ እርግጠኛ የሆነበት ነገር ምንድነው? (ፊልጵ. 1፥5-6)

2. "መልካም ሥራን" በሕይወታችን የሚጀምረውና ጥሩ ፍጻሜ እንዲኖረው የሚያደርግ ማን ነው?

3. ትክክል ያልሆኑ የክርስትና ሕይወት አቋሞች፥

   (ሀ)

   (ለ)

4. እንደገና ስለመወለድ ኢየሱስ ምን አለ? (የዮሐ. 3፥3)

5. አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የማያድጉበት ምክንያት ምንድነው?

6. መጽሐፍ ቅዱስ "ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ይጀምራል" ያለበት ምክንያት ምንድነው?

7. ጳውሎስ *"ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመለስበት ቀን"* ሲል፥ ምን ማለቱ ነው?

8. ጳውሎስ ማደግ ስላቃታቸው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ምን ይላል? (1 ቆሮ. 3፥1-2)

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...


1. "እግዚአብሔርን የማመሰግንበት ምክንያት አለኝ" የምትልባቸውን/የምትዪባቸውን ነገሮች ዘርዝር/ዘርዝሪ።

2. “በክርስትና ሕይወቴ እንዳላድግ ዕንቅፋት ሆነውብኛል” የምትላቸውን/የምትዪአቸውን ምክንያቶች ጻፍ/ጻፊ።

3. እነዚህን ዕንቅፋቶች ለማስወገድ መውሰድ አለብኝ የምትለውን/የምትዪውን እርምጃዎች ጻፍ/ጻፊ።

4. ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደግ ማድረግ ያለበት ነገር ምን እንደሆነ በዝርዝር ጻፍ/ጻፊ።

5. እንደገና ባንወለድም በልማድ ብቻ ልንፈጽማቸው የምንችላቸው መንፈሳዊ ልምምዶች ምንድናቸው?



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

**Ethiopian Outreach Ministry**
**P.O.Box 2241**
**York, PA 17405**
**U.S.A.**
**Phone/Fax: (717)846-2041**
**E-Mail: eomusa@aol.com**
**Internet Address:**
**www.ethiopianoutreach.com**

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድራሻ